**ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢ.ጋን)**

የካቲት 20፣ 2004 ዓም

# የቱ ይቅደም?

## በፍቅር ብዛት ኢትዮጵያን የመታደግ ጥሪ!!

የትግል ተዋረዱና መስተጋብሩ በወጉ ሲበጅ አይናጋም። ቅድሚያ ማመንና ላመኑበት ትግል ህይወት እስከመስጠት የሚያደርስ ስንቅ መያዝ ያስፈልጋል።ከቀድሞ ስህተቶች በመማር አዲስ የትግል ስልት በማዋቀር የመታገያውን መሰረት ማጠንከር ግድ ነው። አንዱ በሌላው ላይ የመደራረብ፣ የመጠላለፍ፣ የመፈራረጅ፣ቀለም የመቀያየር፣ የመከፋፈል፣ የመወነጃጀል፣ የሃሳብ ልዩነትን ያለማክበር፣ እኔ ብቻ ባሰፋሁልህ መለያ ተዋብ፣ እኔን ብቻ አዳምጥ ወዘተ የሚሉት አስተሳሰቦች ትግሉንና የትግሉን ቤተሰቦች አስኮርፈዋል፤ አሳዝነዋል። ተስፋ ያስቆረጡበት ጊዜያትም በርካታ ናቸው።

ትግሉን አስተካክሎ፣ መሰናክሎቹን ለመቅበር በዋናነት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው በሰብዓዊነት መዋደድ፣ በአላማ መያያዝ፣ በህብረት መጓዝ፣ ልትፈጠር የሚገባትን አዲሲቷን ኢትዮጵያን በማለም መታገል፣ በመከባበር ላይ የተመሰረተ ውህደት በመመስረት የቀዘቀዘውን የትግል ስሜትና በተስፋ መቁረጥ ያፈገፈጉትትን ዜጎች ወደ ትግሉ መመለስ ለአፍታም ቢሆን ቸል ሊባል የሚገባ ጉዳይ አይሆንም። በተለያዩ ጊዚያት ተስፋ የተጣለባቸው እንቅስቃሴዎች ለምን ይከስማሉ? ምን ማድረግ ይሻላል? የምንከፋፈለውና ለጠላት የምንመቸው እስከመቼ ነው? መሪዎችቻን ሕዝቡ በቅንነት የሚያገለግሉበት ጊዜ መቼ ይሆን የሚመጣው? የሚሉት ጉልህ ጥያቄዎች በበርካቶች ዘንድ የሚነሱ፣ ነገር ግን ምላሽ ያላገኙ ናቸው።

የካቲት 10ቀን 2004 ዓ ም በኑረምበርግ ጀርመን የተካሄደው ስብሰባ ተሳታፊዎች ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ የሚዲያና የህዝብ ግንኙነት ክፍል በሰጡት አስተያየት **"በፍቅር ብዛት ኢትዮጵያን እንታደጋት"** ብለዋል። የጋራ ንቅናቄያችን ዋና ዳይሬክተር አቶ አባንግ ሜቶም **"ኢትዮጵያዊነት ጸሎታችን ይሁን፤ ራሳችንን መርምረን ከልብ እንዋደድ"** ሲሉ የጉባኤተኞቹን ሃሳብ አድምቀውታል።



**የጉባዔው ጠሪና ባለቤት "የፖለቲካና የሲቪክ ማኅበራት አባላት አንድነት ድርጅት" በሚል ስያሜ ይታወቃል። ተቀማጭነቱ ጀርመን ኑረምበርግ ነው።** ከተቋቋመ አስራ ስምንት ወራት አስቆጥሯል። የተለያዩ እምነትና የፖለቲካ አስተሳሰብ ያላቸው ያቋቋሙት ይህ ጥምረት አመራሮቹ ሙሉ በሙሉ ከሰላሳ ዓመት በታች የሆኑ ወጣቶችና ቀደም ሲል በፖለቲካው ዓለም ጎልተው የማይታወቁ ናቸው። "መክረንና

**ዘክረን ኢትዮጵያን ከወደቀችበት አዘቅት እናውጣ” በማለት ባዘጋጁት ስብሰባ ላይ በተጋባዥነት የተገኙት አቶ ኦባንግ ሜቶ ላቀረቡት ጥሪ የተሰጠው ምላሽ “አብረን እንሥራ፤ የጋራ ንቅናቄው መስመር ያዋጣል”** የሚል ነው።

**“...ኢትዮጵያን ከወደቀችበት አዘቅት ለማውጣት መክረንና ዘክረን እንነሳ።ለሰብዓዊነት ቅድሚያ በመስጠት በፍቅር ብዛት የዘረኝነትና የጎጠኝነት ወጥመድ እንበጣጥስ። በፍቅር ብዛት ኢትዮጵያን እንታደጋት። ኢትዮጵያ አገራችን ታማለች። መፍትሄዋ ያለው በኛ በልጆቿ እጅ ነው...” የሚለው ታላቅ ሃሳብ ከስብሰባው ያገኙትና ልቤን የነካው ንግግር ነው ያሉት እንደዜጋ የጀርመን ኢትዮጵያውያን መረዳጃና መገናኛ ማዕከል አባልና የስብሰባው ተሳታፊ ቄስ ግርማ አበበ ናቸው።**

የዕለቱን ስብሰባ የመሩትና የስብሰባውን አዘጋጆች በማማከር ያገለገሉት አቶ ተፈሪ አበጋዝ በበኩላቸው አስተያየታቸውን የጀመሩት “ታላቅና የከበረ መልዕክት ያለው ስብሰባ” በማለት ነበር። **“...በፍቅርና በጽናት እንቁም፤ ኢትዮጵያ ነጻ እንድትወጣ በፍቅር እንጽና፤ በመሸካከም እንሩጥ፤ በመተማመን እንትጋ፤ በታሪክ፣ በባህልና በእምነታች ያስተሳሰሩንን በጎ ነገሮች በመጠበቅ የፍቅራችንን መሰረት እናጥብቅ፤ ለእምነታችንና ለቆምንለት ዓላማ ባሪያ በመሆን ትግላችንን ከሚሸረሽሩ እንጠብቅ...”** የሚሉት አንኳር ጉዳዮች የራሳቸው እምነትና ከስብሰባው ያገኟቸው ቁም ነገሮች ነበሩ።

በስብሰባው ላይ ከሶስት መቶ በላይ ሰዎች ተገኝተዋል። የመሰብሰቢያው አዳራሽ ሞልቷል። የጋራ ንቅናቄያችን ዋና ዳይሬክተር “ልዩ ስሜት ፈጠረብኝ” ያሉት ጉባኤ የተሳታፊዎች መብዛት ብቻ ሳይሆን ከተሳታፊዎች የቀረቡት ሃሳቦችና የስብሰባው መንፈስ ፍጹም የተለየ እንደነበር ይገልጻሉ። “እኔ የፖለቲካ ንግግር አላደረኩም” የሚሉት አቶ ኦባንግ፣ ለጎሊና፣ ለልብና የግል ምላሽ ስለሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ማውሳታቸውን፣ ይህንንም ያደረጉት ከመታገያ መርሃቸው በመነሳት እንደሆነ ይናገራሉ። “በጉባኤው የነበሩትን ሰዎች አላውቃቸውም። ስማቸውንም ልጠራ አልችልም። እምነታቸውና የፖለቲካ አቋማቸውንም አልተረዳሁም። አንድ ነገር ግን አውቅ ነበር። እሱም ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን!!”



በህወሃት/ኢህአዴግ ጥንካሬ ሳይሆን የዜጎች ድካም በማየሉ አገራችን አሳሳቢ ደረጃ ላይ የመገኘቷ ሚስጥር በኢትዮጵያውያን ርህራሄን መሰረት ያደረገ ትስስርና የርስ በርስ ፍቅርን ያስቀደመ አንድነት መፍትሄ እንደሚያገኝ ያስረዱት የንቅናቄያችን መሪ ለልጅ ልጆቻችን ሰቆቃ ማስተላለፍ ይቆም ዘንድ ስደትንና ካገር በመኮብለል የሚገኝን የማንነት ኪሳራ እንደ ዋና ግብ መመልከት ይቁም። በመዋደድ ልዩነታችንን እንቅበር” የሚል ጥሪ አስተላልፈዋል።

በጉባኤው ላይ ግጥሞች ያቀረበችው ወይዘሪት ፀሃይ አበጋዝ የአቶ ኦባንግን ሃሳብ ከሚጋሩት አንዷ ናት። ከብሔር ባነሰ በቀበሌ መቧደን ደረጃ መደረሱ ታላቅ የማንነት ኪሳራ መሆኑን ያወሳችው ገጣሚ በፍቅር ላይ ያልተመሰረተ ቤተሰብ እንደሚፈርስ አመልክታለች። አያይዛም “ከቁሳዊ ርዳታና ድጋፍ ይልቅ ለፍቅርና በፍቅር ላይ የተመሰረተ የዓላማ ፅናት መቅደም አለበት። ከተፋቀርን ቁሳዊ የትግል ግብአቶችን ከማበርከት በላይ ውድ የሆነውን ህይወታችንንም ለመስጠት ያያዘን ፍቅርና የፍቅሩ መሰረት የሆነው ዓላማ ያስገድደናል” ብላለች።

**“ሰው ለሚወደው ነገር ይሞታል” የምትለው ወ/ት ፀሃይ፣** ከስጋና ደምን በላይ በልብ ውስጥ የሚታተም የዓላማ ፅናት ካለ በማንኛውም ዓይነት መደለያና ስብከት የመነዳቱ የቀድሞ በሽታ እንደሚፈወስ አጠንክራ ተናግራለች። **“በአምልኮ ቦታ ሳይቀር ተለያይተናል። በጎሳና ከጎሳ በታች ወርደን ተቧድነናል። ሰላምታ መቀያየር ያቆምን አለን። በጥላቻ ስብከት ተነድተን ማንነታችንን የረሳንና**

**የወደፊቷ አገራችን እድል ያልገባን ብዙ ነን። ቤተሰብን የሚበትነው የፍቅር ርሃብ ትልቅ የሆነውን አገር እንዴት እያመሰው እንደሆነ ያልተገለፀልን እንበረክታለን።በዚህ ሁሉ ልዩነታችን ላይ ቆመን ለመታገልና አገራችንን ለማዳን እንደክማለን።አንዱ ሲያስር ሌላው እየፈታ ትግሉ በራሳችን ድካም ተጓተተ። ይህንን ታሪክ ለመቀየር የምንችልበት አጋጣሚ የመፍጠር ታሪካዊ ግዴታ አለብኝ። ያለ ማንም ቀስቃሽ በመከፋፈል መቃብር ላይ ለመቆምና በፍቅርን በእምነት ላይ የተመሰረተ ትግል እንዲጀመር የምሰራበትን ኃይል ከስብሰባው ወስጃለሁ። እንዋደድ፤ እንያያዝ፤ ኢትዮጵያን እናትርፍ"** በማለት ወ/ት ፀሃይ ጠንካራ አስተያየቷን ሰጥታለች።

የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ጋራ ንቅናቄ መርህ የሆነው ሰብዓዊነትን ያስቀደመ የትግል መስመር ላስመሳዮች ልቦና የሚሰጥ፣ ልባቸው የሸፈተባቸውን ዜጎች ያለ አንዳች መሸማቀቅ ወደ ልባቸው እንዲመለሱ የሚያደርግ በመሆኑ እንደምትደግፈውም አስታውቃለች። ከስብሰባው መጨረሻ ለልቤ ቀርቶልኛል ያለችውን ለሌሎች እንደምታካፍል ለራሷ ቃል መግባቷንም አመልክታለች።

ቄስ ግርማም የፀሃይን ሃሳብ ያጠናክራሉ። ዘረኝነት፣ መከፋፈልና መጠላለፍ ባሪያ እንዳደረገን የሚገልፁት ቄስ ግርማ አገራችን ተበጣጥሳ ክብሯን እንድታጣ የተደረገው በሁላችንም ጥፋት የተነሳ በመሆኑ ከዘረኝነት ይልቅ ለሰብዓዊነት ቅድሚያ በመስጠት ሁሉም ወገኖች የህሊናቸውን መሰረት እንዲያበጁ መክረዋል።

በሃይማኖት አባትነታቸው በጎ የተመኙት ቄስ ግርማ የጋራ ንቅናቄያችን በሁሉም መንገድ የሚጠነክርበትን መንገድ ከሚያፈላልጉት መካከል አንዱ ለመሆን ሙሉ ፈቃደኛነታቸውን ገልፀዋል። በሌላም በኩል በስብሰባው ወቅት ባዩት እንግዳ የሆነ ስሜትና የመግባባት መንፈስ መርካታቸውን አውስተው ቀጣይ ታሪካዊ ስብሰባዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ይካሄዳሉ የሚል እምነት እንዳላቸው ይፋ አድርገዋል።



አቶ በላይ ወንዳፍራሽ የ"እንደዜጋ" አባልና የስብሰባው አዘጋጅ ኮሚቴ አባል ናቸው። የስብሰባውን አስፈላጊነት በማስቀደም ነበር አስተያየታቸውን የሰጡት። እንደሳቸው አገላለፅ ኢትዮጵያዊያን በተለያዩ ምክንያቶች ተራርቀዋል። በስደት ላይ እየኖሩ ለተጨማሪ ስደት ተዳርገዋል። አይፈላለጉም፤ አይረዳዱም፤ በአንድነት ባገራቸው ጉዳይ ላይ ያገባናል ማለት አልቻሉም። ይህንን ልዩነት ለመስበር የተቋቋመው ድርጅት ስብሰባውን ለማዘጋጀት ሲያስብ መነሻው የተበታተነውን አስተሳሰብና ሃይል በማሰባሰብ አንድነት መመስረት፣ እውነተኛ መተሳሰር የሚፈጠርበትን አግባብ ማፈላለግ ነበር።

በጀርመን አገር ከሚሰሩ የሰብዓዊ መብት አካላት ጋር በመዋሃድ የተዘጋጀው ስብሰባ አቶ ኦባንግ እንዲገኙ ሲጋብዝ በሙሉ ድምጽ ያለ ልዩነት ነበር። **አቶ በላይ እንደገለፁት አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ የጀርመን የውጭ ጉዳይ መስሪያ ተወካይ፣ ከጀርመን አካዳሚ፣ የህግ ባለሙያዎች፣ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮችና የኢትዮጵያ ወዳጅ የጀርመን ዜጎች በስብሰባው ከተገኙት መካከል ናቸው።** በጀርመን ጋዜጦች ሰፊ ሽፋን የተሰጠው ይህ ስብሰባ ከዋናው ስብሰባ ቀደም ብሎ ጋዜጣዊ መግለጫ ክፍለጊዜ የነበረውና የተለያዩ ሃላፊነት ላላቸው የጀርመን ዜጎች በቂ ግንዛቤ የተሰጠበት ነበር።

ስብሰባውን ያዘጋጀው ድርጅት የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ወጣት አማን አበጋዝ በበኩሉ ጉባኤው ወትሮ ሲደረጉት ከነበሩት ስብሰባዎች የተለየ እንደሆነበት አስታውቋል። የፖለቲካና የሲቪክ ማህበራት አባላት አንድነት ድርጅትን ያቋቋሙት የተለያዩ ድርጅቶችና ፓርቲዎች ውስጥ የነበሩ መሆኑን

አመልክቶ፣ ድርጅቱ ሲቋቋም “**ያረጀ ርዕዮተ አለም፣ የማይንቀሳቀስ አስተሳሰብና የማያሳትፍ አካሄድን**” ለማስቀረት ታስቦ መሆኑን ተናግሯል።

**“በኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህል አዳዲስ ፊት ማየት አልተለመደም ወይም አይፈለግም” የሚለው አማን፣ “ይህ በሽታ በገዢው ፓርቲ ብቻ ሳይሆን በተቃዋሚ ፓርቲዎችም ውስጥ ያለ በመሆኑ አንድ ቦታ ላይ መቆም ይገባዋል። ወጣቱ የመሥራት አቅም አለው”** ሲል የቀደሙት ልምዳቸውን ለአዲሶቹ በማካፈል ተተኪ ፖለቲከኞችን የማዘጋጀት ሥራ ሊሰሩ እንደሚገባ አስምሮበታል።

እንደ ድርጅትም ሆነ እንደ ግለሰብ ብዙ ሥራ መስራት በሚቻልበት ወቅት ላይ ባሉበት በአሁኑ ወቅት የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ በሩን ስለከፈተላቸው እንደተደሰቱ የገለፀው የድርጅት ጉዳይ ሃላፊ፣ ከጋራ ንቅናቄያችን ጋር በቀጣይ ለመስራት አቋም መያዙን አልሸሸገም። ሲያብራራም “አቶ ኦባንግ የተነሱበት የትግል አቅጣጫና የመታገያ መርህ አርአያችን ነው። ከሳቸውና ከጋራ ንቅናቄው አመራሮች ጋር አብረን የምንሰራበት ምክንያትም ይኸው ነው” ብሏል።

አቶ ወንዳፍራሽም ከወጣት አማን ሃሳብ ጋር ይመሳሰላሉ። የእንደዜጋ አባል የሆኑት አቶ ወንዳፍራሽ ወጣት አመራሮች ትግሉን መምራት እንዳለባቸው የሚናገሩት በምክንያት ነው። **“ህወሃት/ኢህአዴግን በየመድረኩ መዘረር የሚችሉት የስርዓቱ ሰለባ የሆኑት ወጣቶች ናቸው። የህወሃትን የወደፊት ራዕይ በመበጣጠስና ስደት በቃን በማለት ተባብረው ማስተባበር የሚችሉትም እነዚሁ ወጣቶች ናቸው። ይህንን ስል ግን አንጋፋ መሪዎች አያስፈልጉም ማለቴ አይደለም። ቅብብሎሽ አስፈላጊ እንደሆነ ለማሳወቅና አሁን በጀርመን የተደረገውን የወጣቶች መነሳሳት ለማድነቅ ነው”** ባይ ናቸው።

ስብሰባውን ሲመሩ የነበሩት አቶ ተፈሪ አበጋዝ እንደሚሉት በሰብሰባው ላይ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮችና አባላት ቢገኙም በሚያስገርም ሁኔታ መናበብ ነበር። በሌላም በኩል ከትግሉና ከተሳትፎ ርቀው የነበሩ የትግል ስሜታቸው ተነሳስቷል።

የፖለቲካ አመለካከት ጭቅጭቅ፣ የድርጅቶች የርስ በርስ መገፋፋት፣ የቃላት ጨዋታና መጎነታተል ይኖራል የሚል ግምት ቢኖርም የተለያዩ ፓርቲዎች በውል ሳይስማሙና የዓላማ አንድነታቸውን ይፋ ሳያደርጉ ቀና አቋም ማሳየታቸው የስብሰባው አንዱና ትልቁ ስኬት እንደነበር ያወሱት አቶ ተፈሪ **“ኢትዮጵያዊያን የህወሃት/ኢህአዴግን መከራና ግፍ ከመቁጠር ተላቀን በጉልበትና በፍቅር አገራችንን ነጻ እናውጣ፣ በመሸካከም የተጀመረውን ትግል ከዳር እናድርስ። ከሳትነው አገራዊ አጀንዳ የሚበልጥ ምንም ነገር ስለሌለ አዲሲቷን ኢትዮጵያ ለመገንባት እጅ ለእጅ እንያያዝ”** የሚለው ሃሳብ ከስብሰባው በኋላ በተሳታፊዎችና በአዘጋጆች ልቡና ውስጥ የቀረ የቀጣዩ ሥራ መሰረት እንደሆነ አስረድተዋል።

ያነጋገርናቸው የስብሰባ ተሳታፊዎች የሰጡት ተመሳሳይ ሃሳብ ሆኖ በማግኘታችን የተወሰኑትን ብቻ አቅርበናል። የጋራ ንቅናቄያችን የሚዲያና ህዝብ ግንኙነት ግብረኃይል “ከዚያስ” የሚል ጥየቄ ለወጣት አማንና ለአቶ ኦባንግ አቅርቦ ነበር። **ወጣት አማን “ሥራው ተጀምሯል፤ በተከፈተልን በር ገብተናል” ሲል ከጋራ ንቅናቄያችን ጋር አብረው መስራት መጀመሩን አብስሯል። አቶ ኦባንግ በበኩላቸው “በደስታ የምንቀበለው፣ በሁሉም ዓለም እንዲኖር የምንፈልገው በኅብረትን መነሳሳትን ነው”** በማለት ምላሽ ሰጥተዋል።

“እዚህ ያላችሁ ስደተኛ ኢትዮጵያዊያኖች ያሳለፋችሁትንና ያለፋችሁበትን መንገድ ታውቁታላችሁ? ወረቀት ያላችሁም ሆነ ወረቀት የሌላችሁ በሙሉ በፍቅር የምትኖሩበት አገር አትመኙም? አውሮፓ መድረስ ችግራችሁ ተፈታ ማለት አይደለም። የልጅ ልጆቻችን ወደፊት የሚኮሩበት አገር የመፍጠር ኃላፊነት ተሸክመናል። ሰቆቃና ማንነት የጠፋበት አገር ለአዲሱ ትውልድ ማውረስ አይበቃንም? ከዚህ በላይ እረፍት የሚነሳ ጉዳይ የለብንምና አጅ ለእጅ እንያያዝ። **በፍቅር እንነሳ። ሁላችንም የራሳችንን ድርሻ በቅንነት መወጣት እንጀምር…”** የአቶ ኦባንግ መልዕክት ነበር።

**ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)**

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) የሚዲያና ሕዝብ ግንኙነትን (media@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ*

